የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**Press Release**

## Ethiopian Capital Market Authority Grants Licenses to Five New Capital Market Service Providers

*Addis Ababa, Ethiopia – Friday, March 21, 2025*

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) is proud to announce the granting of licenses to five new capital market service providers (CMSPs) in a significant step toward the development and expansion of Ethiopia's financial markets. The licensing event/ ceremony which took place on Friday, March 21, 2025, marks a historic milestone in Ethiopia's capital market development as we witness the first investment banks in Ethiopia and the total number of licensed CMSPs increase from four to Nine.

The new licensees and their license categories are:

1. **CBE Capital S.C. - Investment Bank**
2. **Wegagen Capital Investment Bank S.C.- Investment bank**
3. **Ethio-Fidelity Securities S.C. - Securities Dealer**
4. **HST Investment Advisory Services PLC - Securities Investment Advisor**
5. **Equation Securities Investment Advisor PLC - Securities Investment Advisor**

These new additions are pivotal to the creation of a more diversified and robust capital market in Ethiopia, providing essential services ranging from investment banking and advisory to securities brokerage and dealing. This development is a strong indication that the Ethiopian capital market is maturing and preparing to serve the growing needs of both local and international investors.

Until now, the Ethiopian capital market has been limited to four licensed service providers, all of which have operated solely as investment advisers. With the inclusion of an **investment bank** and a **securities dealing company**, this expansion represents a transformative moment for the market. These new service providers will contribute to the market's depth and efficiency, allowing for better capital raising and investment opportunities, and introducing much-needed diversity into the financial landscape.

As the Ethiopian capital market grows, so too will the expectations placed on these new service providers. They will be instrumental in building investor confidence, increasing market liquidity, and contributing to the development of capital raising instruments that will benefit both issuers and investors alike.

The licensing of **CBE Capital S.C.** and **Wegagen Capital Investment Bank S.C.** is especially significant because both institutions are substantially owned by two major commercial banks—**Commercial Bank of Ethiopia (CBE)** and **Wegagen Bank**, respectively. These two commercial banks have already been operating under the regulatory framework of the National Bank of Ethiopia (NBE). The banks' ability to invest in capital market services reflects the positive impact of the recently issued **NBE Directive SBB/92/2024 on Limitations on investment of banks**, which permits banks to acquire up to 100% equity in capital market service providers. This regulatory advancement allows the financial sector to expand and diversify its offerings, ultimately benefiting investors and the economy at large.

Notably, this milestone also highlights the increasing role of women in Ethiopia's financial sector, as two of the newly licensed entities—Wegagen Capital Investment Bank S.C. and HST Investment Advisory Services PLC—are led by female CEOs. Their leadership exemplifies the growing inclusivity and diversification of the Ethiopian capital market, reinforcing the importance of gender representation in shaping the country's financial landscape.

In her remarks at the licensing event, in addition to congratulating the new licensees, the Director General (DG) of the Ethiopian Capital Market Authority has emphasized the importance of viewing these new licenses as a **responsibility** to the future of Ethiopia's capital market. The Director General stressed that the new CMSPs must operate with the utmost integrity and commitment, and their role in shaping the market will be crucial to ensuring the success and sustainability of Ethiopia's financial sector.

### A Stronger, More Resilient Capital Market Ahead

The licensing of these five new capital market service providers is a clear sign that Ethiopia is on track to create a **functional, diverse,** and **well-regulated capital market** that will drive the country's economic growth. The Ethiopian Capital Market Authority remains committed to providing the support and regulatory framework necessary for the continued success of the capital market and its participants.
The ECMA also reaffirms its commitment to building a market that can foster innovation, attract investments, and contribute to sustainable economic development. With the growth of licensed CMSPs and the continual enhancement of regulatory frameworks, Ethiopia is positioned to become an increasingly attractive destination for both local and international investors.

### About ECMA

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) stands as a pivotal institution mandated to foster the development and regulation of the capital market within the Federal Democratic Republic of Ethiopia. Established under Article 3(1) of the Proclamation, the ECMA operates as an independent regulatory body with its own juridical identity, reporting directly to the Prime Minister of Ethiopia. Embracing a multifaceted approach, the ECMA is committed to enhancing investor confidence, facilitating capital mobilization, and promoting sustainable economic growth through robust regulatory frameworks and strategic initiatives.
For more information, please visit ecma.gov.et.
**For enquiries & additional information contact**

Saron Woldegabriel
Director, Communications & Public Relations
Phone: 011-5-57-81-62
Email: swoldegabriel@ecma.gov.et

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY
Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**ጋዜጣዊ መግለጫ**

## የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለአምስት አዳዲስ ድርጅቶች የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭ ፍቃድ ሰጠ።

*አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ - ዓርብ ፣መጋቢት 12 ቀን 2017 ዓ.ም.*

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለኢትዮጵያ የፋይናንስ ገበያ እድገት ጉልህ አስተዋፅዖ ሊያደርጉ ለሚችሉ አምስት አዳዲስ ድርጅቶች የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭ ፍቃድ መስጠቱን በደስታ ይገልፃል። ዓርብ መጋቢት 12 ቀን 2017 ዓ.ም የተካሄደው የፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹ የኢንቨስትመንት ባንኮችንና የሰነደ ሙዓለንዋይ ገበያ አከናዋኝ (Securities Dealer) ፍቃድ የተሰጠበት እና አጠቃላይ ፍቃድ የተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን ቁጥር ከአራት ወደ ዘጠኝ ከፍ ያደረገ ነው።

አዲሶቹ ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅቶች እና የተሰጣቸው የፈቃድ አይነት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. **ሲቢኢ ካፒታል አ.ማ - ኢንቨስትመንት ባንክ**
2. **ወጋገን ካፒታል ኢንቨስትመንት ባንክ አ.ማ - ኢንቨስትመንት ባንክ**
3. **ኢትዮ-ፊደሊቲ ሴኩሪቲስ አ.ማ - የሰነደ ሙዓለንዋይ ገበያ አከናዋኝ (Securities Dealer)**
4. **ኤች ኤስ ቲ ኢንቨስትመንት አድቫይዘሪ ሰርቪስስ ኃ.የተ.የግ. ማ - የሰነደ ሙዓለንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪ**
5. **ኢኩቿን የሰነደ ሙዓለንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪ ኃ.የተ.የግ. ማ - የሰነደ ሙዓለንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪ**

የእነዚህ አዳዲስ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ወደገበያው መምጣት በኢትዮጵያ ውስጥ የበለጠ የአገልግሎት ብዝሃነት ያለው ጠንካራ የካፒታል ገበያ ለመፍጠር እንዲሁም ለህብረተሰቡ ከኢንቨስትመንት ባንክ እና ከማማከር አገልግሎቶች ጀምሮ እስከ የሰነደ ሙዓለንዋይ ግብይቶችን የማስፈጸምና የማከናወን ድረስ ያሉ ቁልፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት ወሳኝ ናቸው።

እስካሁን ድረስ የካፒታል ገበያው ፈቃድ ባላቸው አራት የኢንቨስትመንት አማካሪዎች ብቻ ተወስኖ የነበረ ሲሆን፣ ዛሬ የኢንቨስትመንት ባንክ እና የሰነደ ሙዓለንዋይ ገበያ አከናዋኝ ድርጅቶችን በማካተት መስፋፋቱ የገበያው ተሳታፊዎች አዳዲስ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። እነዚህ አዳዲስ አገልግሎት ሰጭዎች ለገበያው ጥልቀት እና ቅልጥፍን የሚጨምሩ ሲሆን ለተሻለ የካፒታል ማሰባሰብ እና የኢንቨስትመንት እድሎችም በር ይከፍታሉ። በተጨማሪም የኢንቨስተሮችን አመኔታ በማጎልበት፣ የገበያ ፍትሃዊነትን በማሳደግ እና የካፒታል ማሰባሰቢያ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ካፒታል ፈላጊ ተቋማትንም ሆነ ኢንቨስተሮችን በእጅጉ ተጠቃሚ ማድረግ ይችላሉ።

በተለይም ሲቢኢ ካፒታል አ.ማ እና ወጋገን ካፒታል ኢንቨስትመንት ባንክ አ.ማ ወደዘርፉ መግባታቸው ጠቀሜታው የጎላ ነው። ምክንያቱም ሁለቱ አዳዲስ ተቋማት በሁለት ትላልቅ የንግድ ባንኮች ማለትም እንደ ቅደምተከተላቸው በየኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በወጋገን ባንክ በከፍተኛ ባለድርሻነት (majority shareholding) የተያዙ ሲሆን ይህም ባንኮች በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ዘርፍ ውስጥ መግባት መጀመራቸው ለገበያው መነቃቃትና እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ሁለቱም የንግድ ባንኮች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የቁጥጥር ማዕቀፍ ስር እንደሚሰሩ የሚታወቅ ሲሆን ባንኮች በካፒታል ገበያ አገልግሎቶች ላይ መሰማራት መቻላቸው በቅርቡ የወጣው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/92/2024 አወንታዊ ውጤት ነው ሊባል የሚችል ሲሆን፣ ይህ መመሪያ ባንኮች በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ውስጥ እስከ 100% ድርሻ በመያዝ በዘርፉ እንዲሰማሩ ፈቅዷል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY
Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

በተጨማሪም የዛሬው ሁነት በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ የሴቶች ሚና እያደገ መምጣቱንም የሚያሳይ ሲሆን ፍቃድ ከተሰጣቸው ድርጅቶች መካከል ሁለቱ ማለትም ወጋገን ካፒታል ኢንቨስትመንት ባንክ እና ኤች.ኤስ. ቲ ኢንቨስትመንት አድቫይዘሪ ሰርቪስስ በሴት ዋና ስራ አስፈጻሚዎች የሚመሩ ናቸው።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ሀና ተኸልቁ በፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓቱ ላይ ባደረጉት ንግግር ለተቋማቱ የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላልፈው አገልግሎት ሰጪዎቹ የተሰጣቸውን ፈቃድ እንደ ኃላፊነትም ጭምር መመልከት እንዳለባቸው አጽንኦት ሰጥተዋል። ዋና ዳይሬክተሯ አዲሶቹ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች የኢትዮጵያን የፋይናንስ ሴክተር ስኬት እና ዘላቂነት ለማረጋገጥ እና ገበያውን ለመቅረጽ የሚጫወቱት ሚና ወሳኝ መሆኑን በማስገንዘብ፣ በሙሉ ቅንነት እና ቁርጠኝነት መስራት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ፈጠራን የሚያበረታታ፣ ኢንቨስትመንትን የሚስብ እና ለዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት ትልቅ ድርሻ የሚያበረክት ገበያ ለመገንባት በሙሉ ቁርጠኝነት እየሰራ ሲሆን ፍቃድ የተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ቁጥር መጨመር እና የቁጥጥርና የሕግ ማዕቀፎችም እየተጠናከሩ መሆናቸው ሀገራችንን ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ኢንቨስተሮች ማራኪ መዳረሻ ለማድረግ የሚያግዝ ነው።

**ስለ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን**

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያን ለማሳደግ እና ለመቆጣጠር የተቋቋመ ሲሆን በካፒታል ገበያ አዋጁ አንቀፅ 3(1) መሰረት ባለስልጣኑ ህጋዊ ሰውነት ያለው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ የሆነ ተቆጣጣሪ ተቋም ነው። ባለስልጣን መ/ቤቱ ኢንቨስተሮች የመጠበቅ፣ የገበያውን ተዐማኒነት የማረጋገጥ ፣ ስርዐታዊ ስጋቶችን የመቀነስ እና ገበያውን የማሳደግ አላማን በማንገብ በጠንካራ የቁጥጥር ማዕቀፎች እና ስልታዊ ስትራተጂዎች እየሰራ የሚገኝ ተቋም ነው።

ለበለጠ መረጃ ድረገጻችንን ይጎብኙ ecma.gov.et

**ለጥያቄዎች እና ለተጨማሪ መረጃ**

ሳሮን ወ/ገብርኤል
የኮምኒኬሽን እና ህዝብ ግንኙነት ሃላፊ
የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን
ስልክ- 011-5-57-81-62
ኢሜል- swoldegabrie@ecma.gov.et